# በኢትዮጵያ የአፍላ ወጣቶች የፅንስ ማቋረጥ ሁኔታ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው ጥናት ይፋ ሆነ

## አፍላ ወጣት ሴቶች ደህንነቱ በተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ተደራሽነት በእጅጉ ተጠቅመዋል

በ1997 ዓ.ም. የተደረገው የፅንስ ማቋረጥ ሕግ መሻሻል ሕጋዊና ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ተደራሽነትን በማምጣቱ አፍላ ወጣት ሴቶች በእጅጉ እንደተጠቀሙ ይህ ጥናት አመላክቷል፡፡ “በኢትዮጵያ የአፍላ ወጣቶች የፅንስ ማቋረጥ ሁኔታ ጥናት” በሚል ርዕስ በጉትማቸር ኢንስቲትዩት እና በአይፓስ ትብብር ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው ጥናት ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 19 የሆኑ አፍላ ወጣት ሴቶች የሚያደርጉትን ደህንነቱ የተጠበቀ ሕጋዊ የፅንስ ማቋረጥ እንዲሁም በድብቅ ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ የሚከናወነውን የፅንስ ማቋረጥ መጠን እና በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ከፅንስ ማቋረጥ ጋር በተያያዘ የሚደርሱ ውስብስብ ችግሮችን ክብደት አካቷል፡፡ ጥናቱ አፍላ ወጣት ሴቶች በዕድሜ ከሚበልጧቸው ሴቶች የተሻለ ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎትን እንደሚያገኙ የጠቆመ ሲሆን ደህንነቱ ያልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ የሚያደርስባቸው ውስብስብ ችግሮች ክብደት በተመለከተ ግን በወጣቶችም ሆነ ወጣት ባልሆኑ ሴቶች መካከል ተመሳሳይ መሆኑን አመልክቷል፡፡

ሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀና ሕጋዊ የፅንስ ማቋረጥ እንዳያገኙ ምክንያት የሚሆኑ እንቅፋቶችን በግልፅ ከቀነሱ ጥቂት ሀገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ እስከ 1997 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ሕግ ፅንስ ማቋረጥን የሚፈቅደው የሴቷን ሕይወት ለማዳን ወይም አካላዊ ጤናዋን ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ነበር፡፡ አዲሱ መስፈርት ግን በመደፈር፣ በሥጋ ዘመዶች መካከል በተደረገ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት፣ ፅንሱ የማይድን የአካል ጉድለት ካለበት፣ በሴቷ አካላዊ እና አዕምሯዊ ዕክል ወይም የወጣቷ ዕድሜ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ የፅንስ መቋረጥን ይፈቅዳል፡፡

በ2006 ዓ.ም. ከነበሩት ፅንስ የማቋረጥ ተግባራት ውስጥ 64 ከመቶ የሚሆኑት በጤና ተቋማት የተደረጉ ደህንነታቸው የተጠበቀ ሂደቶች ነበሩ፡፡ በዕድሜ ትልቅ በሆኑ ሴቶች ከተደረጉ ፅንስ የማቋረጥ ተግባራት ውስጥ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ የተፈፀመው ከአፍላ ወጣቶቹ ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ሲሆን ደህንነቱ ባልተጠበቀ መንገድ የተከናወኑት ደግሞ የበለጡ ነበሩ፡፡ ዕድሜያቸው ከ25

እስከ 29 በሆኑ ሴቶች ከተደረገው ፅንስ ማቋረጥ ውስጥ 46 ከመቶ የሚሆኑት እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ35 በላይ በሆኑ ሴቶች ከተደረገው ፅንስ ማቋረጥ ውስጥ 22 በመቶ የሚሆኑት ብቻ ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ የተከናወኑ ነበሩ:: የተቀሩት ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ የተከናወኑ ነበሩ::

“የኢትዮጵያ የፅንስ ማቋረጥ ሕግ መሻሻል ብዙ ሴቶች ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ እንክብካቤ እንዲያገኙ አስችሏል” ይላሉ ከአጥኚዎቹ አንዱ የሆኑት ዮሐንስ ዲባባ (ዶ/ር):: “አሁንም ግን ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ሴቶች ድብቁን እና ጥንቃቄ የጐደለውን ፅንስ የማቋረጥ ሂደት ለምን እንደሚፈፅሙ ተጨማሪ ጥናት መካሄድ አለበት” በማለት ያክላሉ::

በተጨማሪም በድብቅ በሚፈፀም ፅንስ ማቋረጥ ወይም በፅንስ መጨንገፍ ምክንያት የሚፈጠረውን ውስብስብ ችግር ለማከም የድህረ ፅንስ ማቋረጥ ሕክምና ካስፈለጋቸው ከአራት አፍላ ወጣት ሴቶች ውስጥ አንዷ ከባድ ውስብስብ ችግር እንዳጋጠማት ጥናቱ ይፋ አድርጓል:: ከፅንስ ማቋረጥ በኋላ እንክብካቤ የፈለጉ በዕድሜ ትልቅ የሆኑ ሴቶችም ተመሳሳይ መጠን ያለው ውስብስብ ችግሮች አጋጥሟቸዋል:: ደህንነቱ ባልተጠበቀና ድብቅ በሆነ የፅንስ ማቋረጥ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ ያለፉ አፍላ ወጣት ሴቶች በሕጋዊ መንገድ ፅንስ ካቋረጡ ሴቶች አንፃር ሲታዩ አብዛኛ ዎቹ ያገቡ፣ በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙና የእርግዝና ጊዜው የገፋ ፅንስ ይዘው የመጡ ነበሩ:: የጋብቻ እና የትምህርት ሁኔታ የአፍላ ወጣት ሴቶችን ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት ተደራሽነት እና ተጠቃሚነት ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ለማወቅ ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል::

“በኢትዮጵያ አፍላ ወጣት ሴቶች በሌሎች የዕድሜ ክልሎች ካሉ ሴቶች አንፃር የሚፈጽሙት ፅንስ ማቋረጥ በመጠን ያነሰ ነው” ሲሉ በጉትማቸር ኢንስቲትዩት ከፍተኛ ተመራማሪ እና የአጥኚ ቡድኑ መሪ የሆኑት ኤልዛቤት ሉሲ ተናግረዋል:: “ሆኖም በአፍላ ወጣት ሴቶች ዘንድ ከሚከሰተው እርግዝናዎች ውስጥ ግማሹ ያልተፈለገ ሲሆን ይህም ያልተሟላ የእርግዝና መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን የመጠቀም ፍላጐቶቻቸውን ለማሟላት ብዙ ሥራ እንደሚያስፈልግ ያመለክታል” ብለዋል::

የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ላይ የሚሳተፉ ሴቶች ውስጥ አፍላ ወጣት ሴቶች ከፍተኛ መጠን ያለው ያልታቀደ እርግዝና (ከ1000 ሴቶች ውስጥ 176ቱ) እንደሚያጋጥማቸው ጥናቶች ያመለክታሉ:: ሆኖም ግን በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ላይ ከሚሳተፉ ዕድሜያቸው ከ15-49 በሆናቸው 1000 ሴቶች ውስጥ ያልታቀደ እርግዝና የሚያጋጥማቸው 101 ናቸው:: አፍላ ወጣት ሴቶች ከዕድሜ ከሚበልጡዋቸው ሴቶች ጋር ሲነፃፀሩ ብዙውን ጊዜ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የማያደርጉ ቢሆንም የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን ከመጠቀም አንፃር ግን በርካታ መሰናክሎች አሉባቸው::

አፍላ ወጣት ሴቶች በዕድሜ ከገፉ ሴቶች አንፃር ሲታይ ዝቅተኛ የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተሳትፎ ያላቸው በመሆኑ በአጠቃላይ ባለው የፅንስ ማቋረጥ ምጣኔ ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በ2006 ዓ.ም. ዕድሜያቸው ከ15-19 ካሉ አፍላ ወጣት ሴቶች ውስጥ 96,243 ፅንስ ማቋረጥ ተከናውኗል፡፡ ይህም ከእያንዳንዱ 1000 አፍላ ወጣት ሴቶች ውስጥ 20ዎቹ ፅንስ ያቋርጣሉ እንደማለት ነው፡፡ ሆኖም ግን በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ላይ ተሳትፎ ያላቸውን ሴቶች ብቻ ነጥለን ስንመለከት ዕድሜያቸው ከ15-19 ያሉት አፍላ ወጣት ሴቶች ከፍተኛ የፅንስ ማቋረጥ ምጣኔ ያላቸው ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢዎች ለአፍላ ሴት ወጣቶች የተሟላና ከፍተኛ ጥራት ያለው የእርግዝና መከላከያ አገልግሎት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል በማለት ምክረ ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡

ተጨማሪ ጥናቶችን ማካሄድ ለአፍላ ወጣት ሴቶች ደህንነቱ ያልተጠበቀ ፅንስ ማቋረጥ ሲያከናውኑ የሚችሉባቸውን ምክንያቶችን ለመለየት ይረዳሉ፡፡ ከነዚህ ምክንያቶችም ውስጥ በተዋልዶ ጤና ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት ነፃነት፣ የጤና ተቋማት ርቀት፣ ፅንስ ማቋረጥ አስነዋሪ ድርጊት ሆኖ መታየት፣ እንዲሁም ሴቶች በፅንስ ማቋረጥ ሕግና አሠራር ዙሪያ ያላቸው የግንዛቤ መጠን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት በማስቀረት ሁሉም አፍላ ወጣት ሴቶች አስተማማኝና ደህንነቱ የተጠበቀ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማረጋገጥ እነዚህና መሰል ጥረቶች ቁልፍ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

## ለተጨማሪ መረጃ፡-

- ፅንስ ማቋረጥና የድህረ ፅንስ ማቋረጥ እንክብካቤ፣
  የኢትዮጵያ አፍላ ወጣት ሴቶችን የተመለከተ መረጃ
- የኢትዮጵያ አፍላ ወጣቶች የፅንስ ማቋረጥ ጥናት

የጉትማቸር ኢንስቲትዩት
www.guttmacher.org
ትክክለኛ የጤና ፖሊሲ ተአማኒነት ካለው ጥናት ይመነጫል

## አድራሻ

Facebook: http://www.facebook.com/guttmacher

Twitter: http://twitter.com/guttmacher

Linkedin: http://linkedin.com/company/guttmacher/institute

Tumbir: http://guttmacher.tumbir.com